# የAPS የድጋፍ እና የስኬት ማዕቀፍ

# እያንዳንዱ ተማሪ ዋጋ አለው-ልቀት ለሁሉም

የ 2022-23 በክፍፍል የሚሰጠው ግምገማችን እያንዳንዱ ተማሪ በስም፣ ባለው ጥንካሬ እና በፍላጎቶቹ ማወቅ እና የተማሪዎቹን ዳታ ተጠቅሞ ተማሪዎች ያሉባቸው የ የቋንቋ ክህሎት ችግሮች፣ አካላዊ ጉዳት፣ የተሰጥኦ ፍላጎቶች ወይም ሌሎች ወሳኝ የሆኑ ጉዳዮችን ለመሸፈን ድጋፍ ማድረግ።

## ሁሉም ተማሪዎች ከፍተኛ ጥራት ያላቸው ትምህርቶችን ያገኛሉ።

ሁሉም ተማሪዎች የእያንዳንዳቸውን የመማር ፍላጎቶች ለማሟላት ተብለው የተዘጋጁትን ከፍተኛ ጥራት ያላቸው የክፍል ውስጥ ትምህርቶችን ያገኛሉ። አስተማሪዎች ለተማሪዎች ድጋፍ ዕቅድ ለማውጣት እና እያንዳንዱ ተማሪ ላይ ጥሩ ውጤት ለማምጣት የሚያስችሉ ምርጥ ትምህርቶችን ስራ ላይ ለማዋል በቡድን ሆነው ስብሰባ ያካሂዳሉ። በሁሉም የክፍል ደረጃዎች ላይ፣ የተቀመጡ ግቦችን እያሳኩ ያልሆኑ ተማሪዎች ተጨማሪ ድጋፍ ለመስጠት ቡድኖች ዳታ እና በደረጃ የሚከናወን አቀራረብን ይጠቀማሉ።



**የ ከ 80-85% የሚሆኑ ተማሪዎችን ፍላጎት ያሟላል**

- የግል ጥንካሬዎችን እና ፍላጎቶችን
- ብዝሃነት ያለው፣ አካታች የሆነ እና እንግዳ ተቀባይ የሆነ የትምህርት አከባቢን ለሚሟላት ተብሎ የሚዘጋጅ ትምህርት
- ወሳኝ፣ የፈጠራ አስተሳሰብ እና የግንኙነት ክህሎቶችን ለማዳበር የሚዘጋጁ ተግባራት
- የአነስተኛ ቡድን ተግባራት
- የአካል ጉዳት ላለባቸው፣ የእንግሊዘኛ ቋንቋ ተማሪዎች ለሆኑ እና የተፈጥሮ ዝንባሌ ወይም ስጦታ ላላቸው ተማሪዎች የሚቀርቡ በልዩ ሆኔታ የተዘጋጁ አገልግሎቶች
- Integrated Social-Emotional Learning (SEL) (የተቀናጀ ማህበራዊ-ስሜታዊ ትምህርት) ትምህርቶች እና ልምምዶች
- እንደ አስፈላጊነቱ ከልስ፣ አለማምድ እንደዚሁም መልስህ አስተምር
- ፈተናዎች እና የለውጥ ክትትሎች

ደረጃ 1

## ለተወሰኑ ተማሪዎች ተጨማሪ ድጋፎች ይደረግላቸዋል

በተወሰኑ ቦታዎች ላይ ተጨማሪ ድጋፍን የሚፈልጉ ተማሪዎች ከፍተኛ ጥራት ያላቸው የክፍል ውስጥ ትምህርቶችን የሚያገኙ ሲሆን



**ከ 10-15%የሚሆኑ ተማሪዎች በዚህ ደረጃ የሚሰጥ ድጋፍን ይፈልጋሉ**

+

- ተጨማሪ የ አንድ-ለ-አንድ ወይም የአነስተኛ ቡድን ድጋፍ
- ተደጋጋሚ የመሻሻል ክትትል እና ግምገማ

ደረጃ 2

## የተወሰኑ ተማሪዎች የተጠናከረ፣ የረዥም ጊዜ ድጋፍን ይቀበላሉ

ከክፍል ደረጃቸው አንፃር ከግብ እጅግ በታች የሆኑ ወይም ተለይተው በታወቁ ቦታዎች ላይ የበለጠ ጠንካራ ድጋፍ የሚፈልጉ ተማሪዎች ከፍተኛ ጥራት ያለው የክፍል ትምህርት ይቀበላሉ እንዲሁም



**1-5 %የሚሆኑ ተማሪዎች በዚህ ደረጃ የሚሰጥ ድጋፍን ይፈልጋሉ**

+

- ፍላጎት ባለባቸው ቦታዎች ላይ የ አንድ-ለ-አንድ ወይም የአነስተኛ ቡድን ድጋፎች።
- ተደጋጋሚ የመሻሻል ክትትል እና ግምገማ
- ሪፈራሎች ለተጨማሪ ግምገማ በሚያስፈልጉበት ጊዜ

ደረጃ 3

EVERY STUDENT COUNTS
EXCELLENCE FOR ALL

# የAPS የድጋፍ እና የስኬት ማዕቀፍ
# እያንዳንዱ ተማሪ ዋጋ አለው-ልቀት ለሁሉም




***እያንዳንዱን ተማሪ በስም፣ ባለው ጥንካሬ እና በፍላጎቶቹ እወቀው***

## ቤተሰቦች ምን መጠበቅ ይችላሉ

- ልጇ የክፍል ደረጃውን መለኪያዎች/የሚጠበቁበትን ነገሮች (የሪፖርት ካርዶች፣ የግምገማ መረጃዎች እና መደበኛ ግንኙነት) በማሟላት ላይ ስላለው የእድገት ሂደት መረጃ
- የትምህርታዊ እና/ወይም የባህሪ ስጋቶችን አስቀድሞ መለየት
- የክፍል-አቀፍ እና የትምህርት ቤት ሂደት መረጃዎችን ማተም
- ከልጇ የትምህርት እና/ወይም የባህሪ ፍላጎቶች ጋር የሚዛመድ የክፍል ትምህርት እና የጣልቃ ገብነት ድጋፍ
- ለልጇ በመረጃ ላይ የተመሰረተ ችግር አፈታት ላይ ትብብር እና ተሳትፎ
- ልጇ ለታለመለት ግለሰባዊ ጣልቃገብነት እንዴት ምላሽ እየሰጠ ነው በሚለው ዙሪያ መደበኛ ግብረመልስ
- ለልዩ ትምህርት አገልግሎት በሚያስፈልግበት ጊዜ ከወላጆች/አሳዳጊዎች ጋር በመተባበር የሚሰጡ ሪፈራሎች
- ለወላጆች ግልጽ የግንኙነት መንገዶች: መጀመሪያ የተማሪውን መምህር፣ ከዚያም ሌሎች የት/ቤት ሰራተኞችን እንደ አስፈላጊነቱ ያነጋግሩ።

**የAPS የተማሪ ድጋፍ ዑደት**




## 1 ክትትል እና ግምገማ

APS ተማሪዎች በግል መማሪያ ክፍሎች ላይ፣ ትምህርት ቤቶች ውስጥ እና በስርዓቱ ውስጥ**ምን እንደሚያውቁ እና ምን ማድረግ እንደሚችሉ** በተደጋጋሚ ይከታተላል። ልዩ ድጋፉ እየሰራ መሆኑን ለማወቅ ማጣሪያዎች እና ግምገማዎች ጥቅም ላይ ይውላሉ። APS የተለያዩ **ተከፋፍለው የሚሰጡ ግምገማዎችን** በየ ዓመቱ ያካሂዳል፣ የሚከተሉትን ጨምሮ:

- Dynamic Indicators of Basic Early Literacy Skills (DIBELS) (የ መሰረታዊ የሆኑ የቀደምት የትምህርት ችሎታ ተለዋዋጭ አመልካቾች)
- የንባብ ችሎታ ግምገማ (ከ 6-9ኛ ክፍል፣ በዓመት 3 ጊዜ)
- የሂሳብ ትምህርት ግምገማ (ከ 1ኛ እስከ 8ኛ ክፍል፣ በዓመት 3 ጊዜ)
- የትምህርት መለኪያዎች (SOL) ፈተናዎች (ከ3-12ኛ ክፍል)
- Social-Emotional Learning Screener (የማህበራዊ-ስሜታዊ ትምህርት ማጣሪያ)(ከ 3-12 ክፍሎች፣ በዓመት ለተደጋጋሚ ግዜ)
- Phonetic Awareness (የፎነቲክ ግንዛቤ) የንባብ እና ፅሁፍ ማጣሪያ (PALS)

## 2. ዕቅድ

መምህራን የእያንዳንዱን ተማሪ ፍላጎት እና ጥንካሬ መሠረት ያደረገ ትምህርት ለማቀድ በቡድን ሆነው ይሰራሉ። እነዚህ ዕቅዶች ለሁሉም ተማሪዎች የሚሆኑ በልዩ ሁኔታ የተዘጋጁ ድጋፎ እና ስትራቴጂዎችን የሚያጠቃልሉ ናቸው፣ የሚከተሉትንም ያጠቃላሉ **IEPs/504s ያለባቸው ተማሪዎች፣ የእንግሊዘኛ ቋንቋ ተማሪዎች፣ የስጦታ አገልግሎቶችን የሚቀበሉ ተማሪዎች፣ ነጭ ያልሆኑ ተማሪዎች (ጥቁር፣ ሂስፓኒክ/ላቲኖ፣ ኤገርያዎች፣ ሌሎችም)፣** እና ተጨማሪ/የተለያዩ **ሁለተኛ ደረጃ ላይ ለሚገኙ ተማሪዎች** የሚቀርቡ ድጋፎች። እነዚህ ዕቅዶች የሚከተሉትን የሚያካትቱ ናቸው **Social-Emotional Learning (SEL) (ማህበራዊ-ስሜታዊ ትምህርቶች)** ስትራቴጂዎች እና ሃብቶች።

## 3 ከድጋፍ ጋር ማስተማር

አስተማሪዎች፣ ድጋፍ ሰጪዎች እና የትምህርቲ ስፔሻሊስቶች **እነዚህን የተማሪዎችን ስኬት ለመደገፍ በልዩ ሁኔታ የተዘጋጁ ዕቅዶችን ለመተግበር** ከተማሪዎች ጋር አንድ ላይ ይሰራሉ። አማካሪዎች እና የአእምሮ ጤና ቡድኖች የማህበራዊ-ስሜታዊ ትምህርት ድጋፍ እና ግብዓቶችን ይሰጣሉ።

## 4 በእርጋታ አስብ

መምህራን የተማሪን እድገት ለመገምገም እና እንደ አስፈላጊነቱ የግለሰብ እቅዶችን ለማስተካከል በቡድን በመሆን በመደበኛነት ይተባበራሉ። **ተደጋጋሚ ግምገማዎች እና አስተያየቶች** ለእያንዳንዱ ተማሪ ስኬት ላይ እጅግ በጣም ጥሩ የሆኑ ውጤቶችን ለማምጣት የሚያስችሉ ትክክለኛ ድጋፎች ስራ ላይ መዋላቸውን አረጋግጥ።